# ዜና አመዝኤ

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ፣ ቅፅ 14 ቁጥር 3 መጋቢት 2000



## በዚህ ዕትም ውስጥ

በሶማሌ ክልል የተጀመረው የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦት በተሳካ ሁኔታ እየተካሄደ ነው
ገጽ 2

ብሔራዊ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ከ42 ሺህ ሜ/ቶን በላይ በብድር ሠጠ
ገጽ 3

## ባለፉት ሦስት ወራት ከ361 ሺህ ኩንታል በላይ ምግብ ለዕርዳታ ፈላጊ ወገኖች ተመድቧል

በሱማሌ ክልል እና በኦሮሚያ ክልል በቦረና ዞን ለሚገኙ የምግብ ዕርዳታ ፈላጊ ወገኖች ባለፉት ሦስት ወራት ውስጥ በጠቅላላው 361 ሺህ 912.93 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ተመድቦ በአብዛኛው ተጓጉዞ የተከፋፈለና በመከፋፈል ላይ የሚገኝ መሆኑን ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የንብረት አስተዳደርና ትራንስፖርት ማስተባበሪያ መምሪያ የተገኘ መረጃ ያመለክታል፡፡

ከመምሪያው ከተገኘው መረጃ ለመረዳት እንደተቻለው ለሱማሌ ክልል በመጀመሪያ ዙር ለሁለት ወራት ከተመደበው ጠቅላላ 232 ሺህ 248.93 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 196 ሺህ 467.85 ኩንታል ፣ ወይም 85 በመቶ ፣ በሁለተኛ ዙር ለአንድ ወር ከተመደበው ጠቅላላ 101 ሺህ 878 ኩንታል ውስጥ ደግሞ 50 ሺህ 821.96 ኩንታል ወይም 50 በመቶ ያህሉ በድምሩ 247 ሺህ 288.81 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ በክልሉ አምስት ዞኖች ውስጥ ለሚገኙ 29 ወረዳዎች ተጓጉዞ በአብዛኛው ለዕርዳታ ፈላጊ ወገኖች የተከፋፈለ ሲሆን ቀሪውም በመከፋፈል ላይ ይገኛል፡፡



ለሱማሌ ክልል በሁለት ዙሮች ከተጓጓዘው ጠቅላላ 247 ሺህ 288.81 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 70 ሺህ 573.80 ኩንታል ለጎዴ ዞን ፣ 49 ሺህ 081.25 ኩንታል ለደገሐቡር ዞን ፣ 44 ሺህ 680.16 ኩንታል ለዋርዴር ዞን ፣ 41 ሺህ 025.67 ኩንታል ለቆራሄ ዞን እና 31 ሺህ 928.91 ኩንታል ለፊቅ ዞን የተጓጓዘ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ለሁሉም ዞኖች በሁለት ዙር ከተጓጓዘው ጠቅላላ የምግብ ዕርዳታ ውስጥ 200 ሺህ 323 ኩንታል እህል ፣ 21 ሺህ 034 ኩንታል አልሚ ምግብ ፣ 20 ሺህ 044.5 ኩንታል ጥራጥሬ እና 5 ሺህ 888.76 ኩንታል የምግብ ዘይት መሆኑን የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡

በተመሳሳይም በኦሮሚያ ክልል ቦረና ዞን በተራዘመና ደረቅ ፀሐያማ የአየር ፀባይ ሳቢያ ለምግብ እጥረት ለተጋለጡ ወገኖች ለሁለት ወራት የሚበቃ 27 ሺህ 786 ኩንታል የምግብ ዕርዳታ ወደ ስፍራው ተጓጓዞ ለተረጂ ወገኖች እየተከፋፈለ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም 2 ሺህ

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ህዝብ ግንኙነት የሚዘጋጅ
ስልክ. 5529259
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ ፡ www.dppc.gov.et

ዜና አመዝኤ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲና ተባባሪዎቹ የሚያካሂዷቸውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት እንቅስቃሴዎችንና ሌሎች ተጓዳኝ ተግባራትን የሚዘግብ ወርሃዊ ልሳን ነው



የውሀ ችግር በተከሰተባቸው አካባቢዎች 4 ቦቴዎች ተመድበው ለህዝቡ ውሀ በማከፋፈል ላይ የሚገኙ ከመሆኑም ባሻገር እያንዳንዳቸው 5 ሺህ ሊትር የመያዝ አቅም ያላቸው 14 የውሃ ማጠራቀሚያ ጋኖች በኬር ኢትዮጵያ አማካኝነት ወደ ስፍራው መላኩም ታውቋል፡፡

640 ኩንታል ጥራጥሬ ፣880 ኩንታል ዘይት ተመድቦ በዞኑ ለሚገኙ ተጎጂዎች ለማድረስ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን የዕርዳታ ኘሮግራሞች አፈጻጸምና ክትትል መምሪያ ከተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በዞኑ የውሀ ችግር በተከሰተባቸው አካባቢዎች 4 ቦቴዎች ተመድበው ለህዝቡ ውሀ በማከፋፈል ላይ የሚገኙ ከመሆኑም ባሻገር እያንዳንዳቸው 5 ሺህ ሊትር የመያዝ አቅም ያላቸው 14 የውሃ ማጠራቀሚያ ጋኖች በኬር ኢትዮጵያ አማካኝነት ወደ ስፍራው መላኩም ታውቋል፡፡ የእንስሳት መኖ ችግርን ለማቃለልም በዞኑ ለሚገኙት በድሬ ፣ ደስዮና ድሬ ወረዳዎች ለአጥቢዎች ርቢ እንስሳት መኖ የሚውል 47 ሺህ 830 ቤል ሣርና 5 ሺህ 535 ኩንታል ኮንስትሬት በኦሮሚያ አርብቶ አደር ኮሚሽን ፣ በኬር ኢትዮጵያና በአሜሪካ ህፃናት ድርጅት ቀርቦ ጥቅም ላይ እየዋለ ነው፡፡

## በሶማሌ ክልል የተጀመረው የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦት በተሳካ ሁኔታ እየተካሄደ ነው

በሶማሌ ክልል ካለፈው ህዳር ወር 2000 ዓ.ም ጀምሮ በመካሄድ ላይ ያለው የዕለት ዕርዳታና የሌሎች አቅርቦቶች በተሳካ ሁኔታ መካሄዱ ተገለፀ፡፡

ይህ የተገለፀው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ልዩ ልዩ አካላት ተጠሪዎችና ኃላፊዎች፣ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቶች ግብረ ኃይል ሰብሳቢዎች በተገኙበት የካቲት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የመሰብሰቢያ አዳራሽ በክልሉ አምስት ዞኖች ባለፉት ሦስት ወራት በምግብ፣ በሰዎችና በእንስሳት ጤና፣ በውሀና በግብርና አቅርቦቶች ላይ የተካሄዱትን እንቅስቃሴዎች ለመገምገምና በቀጣይም ሊወሰዱ በሚገባው እርምጃ ዙሪያ ለመወያየት በተካሄደው የጋራ ምክክር ስብሰባ ላይ ነው፡፡



በስብሰባው ላይ የአመዝኤ ዋና ዳይሬክተር አቶ ሲሞን መቻለ ቀደም ሲል በተባበሩት መንግሥታት ድርጅትና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል በተደረሰው ስምምነት መሠረት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች የተውጣጡ ጥምር የመስክ ተቆጣጣሪ ባለሙያዎችን ያካተቱ ሁለት ቡድኖች የዕርዳታ እንቅስቃሴ ወደሚካሄድባቸው ቦታዎች ተሰማርተው ክትትል እያደረጉ መሆኑንና ከማዕከል አስፈላጊው የዕርዳታ ቁሳቁስ ወደ ስፍራው የተላከ መሆኑን አብራርተው የሰብዓዊ ዕርዳታ እንቅስቃሴው ያለበትን ደረጃ በመገምገም ቀጣይ እርምጃ ስለሚወሰድበት ሁኔታ ለመወያየት የምክክር ስብሰባው መጠራቱን ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ ፊደል ሳራሶሮ በበኩላቸው በሱማሌ ክልል የሚካሄደው የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦት እንቅስቃሴ በመንግሥትና በለጋሽ አካላት አማካኝነት በቅንጅት እየተካሄደ መሆኑን ገልፀው በአንዳንድ የዕርዳታ ማደያ ጣቢያዎች ዕርዳታውን በተገቢው ፍጥነት ከማድረስ አኳያ ያጋጠሙ ችግሮች ቢኖሩም ከአካባቢ የመስተዳድር አካላትና በመስክ ከሚገኙ ጥምር ተቆጣጣሪ ቡድኖች ጋር በመመካከር ችግሩን ለመፍታት ጥረት መደረጉን አስታውቀዋል፡፡

በዚሁ ጊዜ የውሀ ሀብት ልማት ሚኒስትር ዲኤታ አቶ አዱኛ ጀቤሳ በመጠጥ ውሀ አቅርቦት በኩል እየተካሄደ ያለውን እንቅስቃሴ አስመልክተው እንደገለጹት ባለፉት ሦስት ወራት አሳሳቢ የውሀ እጥረት ካለመከሰቱም ባሻገር የነበረውን ችግር በክልሉ አቅም ለመፍታት ጥረት ሲደረግ መቆየቱን አስታውሰዋል፡፡



አያይዘውም አሁን ያለው ፀሐያማና ደረቅ የአየር ሁኔታ በቀጣይ በክልሉ ይጥላል ተብሎ የሚጠበቀው የዝናብ ወቅትም የሚቀጥል ከሆነ ከክልሉ በሚቀርበው ዝርዝር የፍላጎት ጥያቄ መሠረት የውሀ ጉድጓዶችን ለመጠገንና አቅማቸውን ለማጎልበት አስፈላጊም ከሆነ ውሀ በቦቴ ለማቅረብ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ተገቢውን ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሚያስተባብረው በዘርፉ የተሰማሩ የተ.መ.ድ አካላትንና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ያካተተው የውሀና ሳኒቴሽን ግብረሀይል ተቋቁሞ ሁኔታውን በቅርበት እየተከታተለ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በጤና ረገድም ወደ ክልሉ ከተሰማሩት ቡድኖችና ከክልሉ ጤና ቢሮ በሚደርሰው መረጃ መሠረት የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የቅርብ ክትትል እያደረገ መሆኑን የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የጤና ግብረ-ኃይል አስተባባሪ ገልፀው እስካሁን ድረስ በወረርሽኝ መልክ የተከሰተ የጤና ችግር አለመኖሩን አስታውቀዋል፡፡ ሆኖም ክልሉ ካለበት የአቅም ችግርና የመሠረታዊ የጤና ተቋማት እጥረት አኳያ ለአስቸኳይ ጊዜ የጤና ችግር እንዳይጋለጥ የዕለት ተዕለት ክትትል ከመደረጉም በላይ ችግሩን በተንቀሳቃሽ የጤና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት አማካኝነት ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ መሆኑም ተብራርቷል፡፡ በምግብ አቅርቦት ረገድ እስካሁን ድረስ ከ300 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብ ዕርዳታ ለአምስት ዞኖች መመደቡና ከዚህም ውስጥ ከ240 ሺህ ኩንታል በላይ መከፋፈሉ ተገልጿል፡፡

በኢትዮጵያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ ኃላፊ ፊደል ሳራሶሮ በበኩላቸው በሱማሌ ክልል የሚካሄደው የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦት እንቅስቃሴ በመንግሥትና በለጋሽ አካላት አማካኝነት በቅንጅት እየተካሄደ መሆኑን ገልፀው በአንዳንድ የዕርዳታ ማደያ ጣቢያዎች ዕርዳታውን በተገቢው ፍጥነት ከማድረስ አኳያ ያጋጠሙ ችግሮች ቢኖሩም ከአካባቢ የመስተዳድር አካላትና በመስክ ከሚገኙ ጥምር ተቆጣጣሪ ቡድኖች ጋር በመመካከር ችግሩን ለመፍታት ጥረት መደረጉን አስታውቀዋል፡፡ በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ መንግሥት ለችግሩ ትኩረት ሰጥቶ ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አካላትና ለተባባሪዎች የሰጠውን ድጋፍና የሰብዓዊ ዕርዳታ አቅርቦቱን በማስተባበር ያስመዘገበውን ውጤት አድንቀዋል፡፡

# ብሔራዊ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ከ42 ሺህ ሜ/ቶን በላይ በብድር ሠጠ

ብሔራዊ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ከጥር እስከ የካቲት ወር 2000 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ባሉት የሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ 42 ሺህ 043 ሜ/ቶን ምግብ በብድር መስጠቱን ከመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር የተገኘ መረጃ ያመለክታል።

ብሔራዊ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ከጥር እስከ የካቲት ወር 2000 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ባሉት የሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ 42 ሺህ 043 ሜ/ቶን ምግብ በብድር መስጠቱን ከመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር የተገኘ መረጃ ያመለክታል።

የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደር በብድር ከሠጠው ጠቅላላ ምግብ ውስጥ 30 ሺህ ሜ/ቶን ለኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት ቀሪውን 12 ሺህ 043 ሜ/ቶን ደግሞ ለዓለም ምግብ ድርጅት የሠጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

በተያያዘም በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ አስተዳደሩ ቀደም ሲል ለተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከሠጠው ምግብ ውስጥ 9 ሺህ 933.94 ሜ/ቶን ተመላሽ መደረጉን የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት አስተዳደሩ በኮምቦልቻ ፣ መቀሌ ፣ ናዝሬት ፣ ሻሸመኔ ፣ ሽኒሌ ፣ ወላይታ ሶዶ እና ወረታ ላይ በሚገኙት ሰባት የማከማቻ መጋዘኖች እስከ የካቲት ወር መጨረሻ ድረስ በጠቅላላው 171 ሺህ 992.36 ሜ/ቶን ምግብ በክምችት ይዟል።



አስተዳደሩ በተለያዩ ቦታዎች በክምችት ከያዘው ጠቅላላ ምግብ ውስጥ ከ41 ሺህ 585.30 ሜ/ቶን በወረታ ፣ 34 ሺህ 492.99 ሜ/ቶን በኮምቦልቻ ፣ 29 ሺህ 632.20 ሜ/ቶን በመቀሌ ፣ 24 ሺህ 565.63 ሜ/ቶን በናዝ ት ፣ 17 ሺህ 686.49 ሜ/ቶን በወላይታ ሶዶ ፣ 12 ሺህ 043.00 ሜ/ቶን በሻሸመኔ እና 11 ሺህ 686.75 ሜ/ቶን በሽኒሌ ማከማቻ መጋዘኖች የሚገኝ መሆኑን ከአስተዳደሩ የተገኘው መረጃ ያመለክታል።